የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ
NATIONAL ELECTION BOARD OF ETHIOPIA

# የኢትዮጵያ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ የክልል ጽ/ቤት ኃላፊዎች

# ምልመላ መመሪያ ቁ.1/2011 ዓ.ም

## መግቢያ

የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁ.1133/2011 ቦርዱ በገለልተኝነት በፌዴራልና በክልሎች ነፃና ትክክለኛ ምርጫ እንዲያካሂድ ሥልጣን ሰጥቶታል፡፡ በአዋጁ አንቀፅ 23 መሠረት የምርጫ ቦርድ በሁሉም ክልሎች ምርጫ የሚያስተባብር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት እንደሚያቋቁም በመደንገጉ፣

የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ማቋቋሚያ አዋጅ ቦርዱን በአዲስ መልክ ያዋቀረ በመሆኑና ከዚሁ አዲስ አደረጃጀት ጋር የሚሄድ የክልል የምርጫ ማስተባበሪያ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችንና ኃላፊዎችን እንደገና ማዋቀር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የክልል ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ኃላፊዎች በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ገለልተኝነታቸውና ሙያዊ ብቃታቸው ከተረጋገጠ የክልል ነዋሪዎች መካከል በቦርዱ ሰብሳቢ አቅራቢነት በቦርዱ የሚሰየሙ በመሆኑ፤

የክልል ማስተባበሪያ ቅ/ጽ/ቤት ኃላፊዎች አመላመልና ቅጥር ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ የሚወሰን መሆኑን የተደነገገ በመሆኑና የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በአዋጅ የተሰጠውን ኃላፊነት እና ተግባር በአግባቡ ለመወጣት እንዲያስችለው በግልጽነት፣በአሳታፊነት እና በተጠያቂነት ላይ የተመሠረተ የክልል ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ኃላፊዎች የምልመላና የቅጥር መመሪያ አውጥቷል፡፡

## አንቀጽ 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ" የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የክልል ቅ/ጽ/ቤት ኃላፊዎች የምልመላና የቅጥር መመሪያ" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## **አንቀጽ 2. የቦርዱ ሥልጣን**

1) በብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ማቋቋሚያ አዋጅ መሠረት ቦርዱ በሁሉም የኢትዮጵያ ክልሎች ምርጫ የሚያስተባብር ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የማቋቋም ሥልጣን አለው፡፡
2) የክልሎችን የቆዳ ስፋት፣ የህዝቡን አሰፋፈርና የመራጮችን ብዛት መሠረት በማድረግ ቦርዱ ለክልል ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ተጠሪ የሆኑ እንደ የአግባብነቱ የዞን እና የምርጫ ክልል ማስተባበሪያ በቋሚነት ሊያቋቁም ይችላል፡፡
3) ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የክልል ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ኃላፊ ገለልተኛነታቸውና ሙያዊ ብቃታቸው ከተረጋገጠ የክልሉ ነዋሪዎች መካከል በቦርዱ ሰብሳቢ አቅራቢነት በቦርዱ ይሰየማል፡፡

## **አንቀጽ 3. የቦርዱ የክልል ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ተግባርና ኃላፊነት**

እያንዳንዱ የቦርዱ የክልል ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ኃላፊ በቦርዱ እንዲሁም እንደ አግባብነቱ በቦርዱ ጽህፈት ቤት ኃላፊ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያና አቅጣጫ መሠረት የሚከተሉት ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡፡

1) በክልል ደረጃ የሚካሄደውን ምርጫ ይመራል፤ ያስተባብራል፤ ይቆጣጠራል፤
2) በሥሩ የሚቋቋሙት ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤቶች ስለሚደራጁበት ሁኔታ ለቦርዱ ጽህፈት ቤት ሀሳብ ያቀርባል፤
3) ለምርጫ የሚያስፈልጉ ሰነዶችና ቁሳቁሶች ለሚመለከታቸው ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤቶችና የምርጫ ክልልና ጣቢያዎች በወቅቱ መድረሳቸውን ይከታተላል፤ ያረጋግጣል፤
4) ከቦርዱ የሥራ ሂደቱ ኃላፊነት ያለው የሥራ አመራር ቦርድ አባል በሚሰጠው መመሪያ መሠረት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የሥነ-ዜጋና የመራጮች ትምህርት ይሰጣል፤ ያስተባበራል፤
5) የመራጮች አመዘጋገብ፤ የእጩዎች አቀራረብና የድምፅ አሰጣጥ ሥርዓት ህጉ በሚፈቅደው መሠረት እየተካሄደ መሆኑን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤ከምርጫ ተያይዘው የሚነሱትን

ቅሬታዎችና ተቃውሞዎች በክልል ደረጃ እየመረመረ ቦርዱ በሚያወጣቸው መመሪያዎች መሠረት ይወስናል፤

6) የክልሉ የምርጫ ሂደትና ውጤት በሚመለከት ለቦርዱ ጽህፈት ቤት ሪፖርት ያቀርባል፤
7) ለምርጫ አፈጻጸም በሚያመች መልኩ አግባብ ያላቸውን መረጃዎች እየሰበሰበና እያጠና በየጊዜው ለቦርዱ ጽህፈት ቤት ሪፖርት ያቀርባል፤
8) ስለሥራው እንቅስቃሴ በየወቅቱ ለቦርዱ ጽህፈት ቤት ሪፖርት ያቀርባል፤
9) የሥራ አመራር ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት በክልል እና በምርጫ ጣቢያ ደረጃና የፖለቲካ ድርጅቶች የጋራ መድረክ እንዲዋቀር ያደርጋል፤ በክልል የሚቋቋሙ የፖለቲካ ድርጅቶች የጋራ መድረክ ያስተባብራል፤
10) የክልሉ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ያቋቁማል፤
11) የቦርዱ ሰብሳቢና የጽህፈት ቤቱ ኃላፊ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

## አንቀጽ 4. <u>የምልመላ መመዘኛ መርሆዎች</u>

1) ቦርዱ ለየክልሉ የቦርድ ቅ/ጽ/ቤቶች ኃላፊዎችን የሚመለምለው የምርጫ ህጉን፣ አግባብነት ያላቸውን ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት በማድረግ ይሆናል።
2) በቅርንጫፍ ጽ/ቤት ኃላፊዎቹ ምልመላና ቅጥር ሂደት ቦርዱ ግልፅነትን፣ ሚዛናዊነትን እና ፍትሐዊነትን መሠረት ያደርጋል፤
3) በየክልሉ ቅ/ጽ/ቤቶች ኃላፊዎች ሲመለመሉ የምልመላ መመዘኛ መስፈርቶቹ የሴቶችን ተሳትፎ ግምት ውስጥ ያስገባ ይሆናል።

## አንቀጽ 5. <u>የምልመላ መመዘኛ መስፈርቶች</u>

በክልል የምርጫ ቅ/ጽ/ቤት ኃላፊነት በዕጩነት የሚቀርቡ አመልካቾች ማሟላት የሚኖርባቸው መስፈርቶች፡-

1) ኢትዮጵያዊ ዜጋ መሆን፣

2) መደበኛ አድራሻው በምርጫ ክልል ውስጥ ሆኖ የፌዴራልና የክልሉን የሥራ ቋንቋ የመናገርና የመፃፍ ክህሎት ያለው፤
3) በአካባቢው ነዋሪ ሕዝብ አመኔታ ያተረፈና መልካም ሥነ ምግባር ያለው፤
4) የማንኛውም ፖለቲካ ድርጅት አባል ያልሆነ
5) በትምህርት ዝግጅት በተለይ በሕግ፣ በፖለቲካ ሳይንስ፣ በህዝብ አስተዳደር፣ በስታቲስቲክሱ፣ በማኔጅመንት፣ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂና ከምርጫ ጉዳዮች ጋር ተዛማጅነት ባላቸው የትምህርት ዘርፎች ቢያንስ በአንዱ የመጀመሪያ ዲግሪ ያለው፤
6) አመልካች የማስተርስ ዲግሪ ያለው ከሆነ የአራት ዓመት የሥራ ልምድ፤ የመጀመሪያ ዲግሪ ያለው ከሆነ ደግሞ የአምስት ዓመት የሥራ ልምድ ሊኖረው ይገባል።
7) የምርጫ ህጉን፣ ደንብና መመሪያዎችን አንብቦ በመረዳት ለሕዝቡ ማስረዳት የሚችል

## **አንቀጽ 6. <u>የቦርዱ ኃላፊነት</u>**

1) ቦርዱ በቂ አመልካቾች/ተጠቋሚዎችን ማሰባሰብ ይችል ዘንድ ሰፊ ተነባቢነት እና ተደራሽነት ባላቸው ጋዜጦች፣ በሬዲዮና ቴሌቪዥን እና ሌሎች ምቹ የመረጃ ሥርዓቶችን ይጠቀማል።
2) ቦርዱ በአመልካቾ ከሚቀርቡለት ማስረጃዎች በተጨማሪ የሚፈልገው መረጃ ካለ የሚመለከታቸውን መ/ቤቶች የሥራ ኃላፊዎች በማነጋገር የጽሁፍ ማረጋገጫ ሊቀበል ይችላል።
3) ቦርዱ በአካባቢው ጽህፈት ቤት ከፍተው በመንቀሳቀስ ላይ ከሚገኙ የፖለቲካ ድርጅቶች ኃላፊዎች ስለ አመልካቹ የፓርቲያቸው አባል መሆን አለመሆን አስፈላጊውን ማጣራት ሊያደርግ ይችላል።
4) የእጩ አመልካቾች/ተጠቋሚዎች ዝርዝር መያዣ እና ሌሎች የተለያዩ ቅፆችን ያዘጋጃል፤
5) ከአመልካቾችና ከጠቋሚዎች የተሰበሰቡ መረጃዎች በማጠናቀር፣አደራጅቶ የማጣራት ሥራ ይሰራል፤

ከቀረቡት አመልቾች/ተጠቋሚዎች ውስጥ ብቃት ያለው ለመለየት የሚያስችል የነጥብ አሰጣጥ መስፈርት በማውጣት እጩ ተጠቋሚዎችን በውጤታቸው መሠረት በደረጃ ያስቀምጣቸዋል።

## አንቀጽ 7. እጩ የሥራ አመራር ቦርድ አባላት ጥቆማ አቀባበል ሥነ-ሥርዓት

1) ቦርዱ ከእጩ አመልካቾች ማመልከቻዎች የሚቀርቡበትን ጊዜ ወስኖ ከአመልካቾች ምን እንደሚጠበቅ በየክልሉ ሰፊ ተደራሽነት ባላቸው የብዙኃን መገናኛ ማስታወቂያ ያስነግራል፤
2) አመልካች ከማመልከቻው ጋር የሚያቀርባቸው ሌሎች ሰነዶች፡-

    ሀ) ለሥራው ለማመልከት ምን እንዳነሳሳው፣ ለሥራው ቢመረጥ በኃላፊነቱ ምን የተለየ አስዋጽኦ ለማድረግ እንደሚችል ለዚህ ሥራ ምን የተለየ ክህሎት እንዳለው የሚገልፅ ካንድ ገጽ ያልበለጠ ፅሁፍ

    ለ) የትምህርት ማስረጃ

    ሐ) የሥራ ልምድ ማስረጃ

    መ) ከሁለት ሰዎች የተፃፉ ስለ አመልካቹ ለሥራው ብቁነት የሚያስረዱ ደብዳቤዎች

    ሠ) ከሁለቱ ደብዳቤዎች አንዱ ስለአመልካቹ የሥራ አፈፃፀም በቅርብ ከሚያውቅ ሰው መሆን አለበት

    ረ) አመልካች ማመልከቻውን የሚቃርበው በአካል በመቅረብ፤ በፈጣን መልዕክት /EMS/፤ በፖስታ ቤት፤ በኢሜል ሊሆን ይችላል፤

ማመልከቻውና ሰነዶቹ በአካል ለማቅረብ የሚፈልግ አመልካች በሌ ፍላሚንጎ አካባቢ በሚገኘው የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ዋና ጽ/ቤት ቀርቦ መስጠት ይችላል፡፡

3) ከግል አመልካቾች በተጨማሪ መሥፈርቱን የሚያሟሉ ብለው የሚያምኑባቸውን ግለሰቦች መጠቆም ይችላሉ፤
4) ቦርዱ በሌሎች የሚጠቆሙ ግለሰቦች ካሉ የተጠቋሚዎቹን ትክክለኛ አድራሻ ከጠቋሚዎቹ ተቀብሎ ተጠቋሚው ፈቃደኛ ከሆነ አስፈላጊ ማስረጃዎች እንዲያቀርብ ያደርጋል፡፡

## አንቀጽ 8. እጩዎች የመለየትና የማጣሪያ ሥልት

1) ቦርዱ በተቀመጠው መስፈርት መሠረት በቀረቡለት ሰነዶች ላይ በመመስረት አስፈላጊውን ማጣራት በማድረግ ከአመልካቾች ውስጥ የክልል ቅ/ጽ/ቤት ኃላፊ ሊሆኑ የሚችሉ አስር /10/ የመጨረሻ እጩዎችን ይለያል፤

2) በተደረገው ማጣራት የተለዩትን አስር ዕጩዎች ቦርዱ ለቃለ መጠይቅና ለመጨረሻ ማጣሪያ ያቀርባቸዋል፤
3) አሥሩን ለመጨረሻ ማጣራት የቀረቡት ዕጩዎችን በተመለከተ ቦርዱ ሊጣሩ የሚገባቸው ሁኔታዎች ሁሉ በቃለ መጠይቅ በጥልቀት ያጣራል።
4) ቦርዱ አስፈላጊ ሆኖ ካገኘ የአስሩን ዕጩዎች የኋላ ታሪክ የሥራ አፈፃፀም እና ሌሎች አጋዥ የሆኑ መረጃዎች ያጣራል።
5) ለመጨረሻው ማጣራት የቀረቡትን ዕጩዎች በተመለከተ ቦርዱ በአካባቢው ጽህፈት ቤት ከፍተው በመንቀሳቀስ ላይ የሚገኙ የፖለቲካ ድርጅቶችን በማማከር ያላቸውን ሀሳብ ሊጠይቅ ይችላል፤
6) ከመጨረሻ ማጣራት በኋላ በሁሉም መስፈርቶች ከፍተኛ ነጥብ ያገኘ ዕጩ ተወዳዳሪ በቦርድ የክልል ቅ/ጽ/ቤት ኃላፊ ሆኖ ይሰየማል።

## አንቀጽ 9. <u>የሥራ ኃላፊው የሥራ ዘመን</u>

የአንድ የቅ/ጽ/ቤት ኃላፊ የሥራ ዘመን ስድስት ዓመት ይሆናል።

## አንቀጽ 10. <u>መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ በቦርዱ ከፀደቀበት ከነሐሴ 15 ቀን 2011 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ብርቱካን ሚደቅሳ

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ

ሰብሳቢ